የ፳፻፪ ትክክለኛ ምርጫ ልሣን
ምርጫው በጎዥው ክፍል ተዘጋጅቷል።
ሕዝቡ ያለውዴታው ይሣተፋል።
የእኛም አስተዋፅዖ እነሆ።

# እስከመቼ

የካቲት ፳፩ እስከ የካቲት ፳፯ ቀን ፳፻፪ ዓ. ም.
February 28 to March 6, 2010
ቅፅ ፩ ቁጥር ፯
Volume I Number 7

## ኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል

የኤርትራ ጉዳይ ሲነሣ፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ብዙ ጥያቄዎች ከፊቱ ይደቀናሉ። እኛም የዚሁ ስብስብ አካል ስለሆን፣ ጥያቄዎቹ የኛም ስለሆኑ እስቲ እንዘክራቸው። ከወዲሁ ግልፅ ለማድረግ፣ በ*እስከመቼ* ወገን ላለነው፣ የአሰብ ጉዳይ ወይንም ኢትዮጵያ ያለ ባህር በር መዘጋቷ ከጥያቄዎቻችን መካከል አይደሉም። ጥያቄዎቻችን፣ ኤርትራ እንዴት ተገነጠለች? የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ አሁን በምን ዓይነት ኑሮ ውስጥ ነው ያለው? የወደፊት ኑሮውስ? በኢሕአዴግና በሻዕቢያ አመራር መለስና ኢሳያስ በሥልጣን ላይ ሆነው ሕዝባዊ መፍትሄ ማግኘት ይቻላል ወይ? በትግላችን ወቅት የኤርትራ ሚና ምንድን ነው? አንዱን መሪ ተጠቅሞ ሌላውን መሪ መጣል ይቻላል ወይ? አሁን በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል? ለወደፊቱስ ምን መሆን አለበት?

ለነኝህ ጥያቄዎች አንድ ዓይነት መልስ የለንም። አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን አሥመራ ድረስ በመሄድ ኢሳያስ አፈወርቂን ያቀፉ አሉ። በአንፃሩ ደግሞ አዲስ አበባ ድረስ ሄደው መለስ ዜናዊን ያቀፉ ኤርትራዊን አሉ። የዛሬዋ የ*እስከመቼ* ቁጥር ፯ ይህንን ጉዳይ ከትግሉ ወደፊት መጓዝ አንፃር ታየዋለች።

<u>**ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ!**</u> የኢትዮጵያና የኤርትራ ጉዳይ ባንድ ወቅት የፖለቲካ ነፋስ ሸውታ ወይንም አጭር ጥቅም የሚስተናገድና የሚወሰን አይደለም። ስንቶቻችን ነን ዛሬ ካለንበት የታሪክ ውጤት ተነሥተን፣ አፄ ሚኒሊክ መረብ ላይ ባያቆሙ ኖሮ ዛሬ (በወቅቱ የነበሩበትን በውል ሣናሥተባቃ) . . . እያልን ታሪክ አዳሽ የሆነው?

**ለኤርትራ ቀሪው ኢትዮጵያዊ ነፃነቱን ሲያስከብር የፖለቲካ መፍትሄ ይፈልጋል።**

በሚገርም አኳኋን ኢሳያስ አፈወርቂን በመደገፍ ሰላማዊ ሰልፍ ያደረጉ አሉ። አሁንም ኢሳያስ መሣሪያ ሠጥቶ፣ ምሽግ አደላድሎ፣ መለስን እንድንጥለው ይረዳናል ብለው እጅ የሚነሱት አሉ።

እስኪ ራሳችንን እንጠይቅ! ይህ ትግል የማን ነው? ታጋዩ ማነው? ይህ ነው ለኛ ከላይ የተጠቀሱት መሠረታዊ ሥህተት እየሠሩ ነው የሚስብለን። **እምነት በሕዝቡ ማጣት!** ይህንን ደግሞ ሕዝቡ ነፃነቱን ለማስከበር ትጥቅ ከማንሳቱ ጋር ማዛመድ ስህተት ነው። **ሕዝብ ነፃነቱን ለማስከበር ትጥቅ ማንሳቱ ምንጊዜም የተጠበቀ ነው። የማንንም ቡራኬ ወይንም ሕጋዊ ፍቃድ አይጠይቅም።** ይኼንን ሕዝቡ የሚመርጠው፣ ዘለቄታዊና ትክክለኛ መፍትሄ ለማምጣት በአንድነትና በአንድ ፊት ሲነሣ ነው። ዓለም አቀፉዊውን የፖለቲካ አሰላለፍ አመዛዝኖ፣ የራሱንና የጠላቱን ደካማና ጠንካራ ጎን በደንብ አጥንቶ፣ የትግሉን ግብና ሂደት ተልሞ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሁሉን የአንድነት ኢትዮጵያዊ ኃይሎችን በአንድነት ይዞ የሚነሣ ኃይል እውነተኛ መፍትሄ ያመጣል።

በአሁኑ የዓለም ፖለቲካ ሃቅ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን አፈር ለማስጋጥ ድንበርተኛ ደንባራ መንግሥት አይሻም። አንድነቱን እንጂ! መታገያና ምሽጉ ውጭ ሀገር አይደለም። ከተማውና ገጠሩ እንጂ! የኢትዮጵያ ሕዝብ የውስጥ ጠላት ኢሕአዴግና መለስ ከወያኔያዊ አመለካከታቸው ጋር ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር አንድ የውጭ ጠላት ደግሞ፣ የኤርትራዊያን ውስጣዊ ጠላት የሆነው ኢሳያስ አፈወርቂና ሸዐቢያ ናቸው። ኤርትራዊ ወገኑን የሚወድ ኢትዮጵያዊ ከኢሳያስ ጎን አይሰለፍም። **ዴሞክራሲያዊ አመለካከት ያለው ኢትዮጵያዊ፣ ለግል ጥቅሙ ተሠልፎ ኢትዮጵያዊ ሆነ ኤርትራዊ ወገኑን ለመሰዋዕትነት ካልሸጠ በስተቀር ከኤርትራው አምባ ገነን ጎን አይቆምም!**

**የእስከመቼ ዕትም የዝግጅት ቦርድ፣**
ድረስ ነጋ፣ ሕሊና ነጋሣና፣ ሀገሬ ተመቼ
eske.meche@yahoo.com